# ስለምዘናዎች ወይም ፈተናዎች የወላጆች መመሪያ

*ለ2018-19 የትምህርት ዘመን*

**PSAT (ተቀዳሚ የትምህርታዊ ዝንባሌ /ፕሪሊሚናሪ ስኮላስቲክ አፕቲቲዩድ/ ፈተና)**

ምዘናዎች ወይም ፈተናዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ባለሙያዎች (አስተማሪዎች) ተማሪዎች የየክፍል ደረጃቸውን እውቀት (ይዘት) ስለማወቅ አለማወቃቸው እና ለ21ኛው መ/ክ/ዘ ዝግጁ ሆነው ለመመረቅ ስለመቻል አለመቻላቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። የምዘና ውጤቶቹ የልጅዎ ትምህርታዊ ዕድገት/ለውጥ በጥቅሉ ከሚያሳዩት ምዘናዎች አንድ መለኪያ እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው።

## ይህ ምዘና/ፈተና ምንድን ነው?

የPSAT ወይም ተቀዳሚ የትምህርታዊ ዝንባሌ ፈተና ለዘጠንኛ እና ለአሥረኛ ክፍል የኮሎራዶ ስቴት አጠቃላይ የቋንቋ ጥበባት እና ሒሳብ ምዘና ነው። በኮሌጅ ቦርድ የተዘጋጀው PSAT ከኮሎራዶ ትምህርታዊ ደረጃዎች (አካዳሚክ ስታንዳርድስ) ጋር የተጣጣመ እና የተማሪዎችን የንባብ፣ ጽሕፈት እና ቋንቋ እንዲሁም ሒሳብ የብቃት ደረጃዎችን የሚለካ ነው።

የዘጠንኛ ክፍል ተማሪዎች PSAT 9ን ይወስዳሉ። የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች PSAT 10ን ይወስዳሉ። ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ የስቴት ፈተናዎችን በክፍል ደረጃ ያሳያል፦

| | |
|---|---|
| ከ3ኛ - 8ኛ ክፍሎች | የኮሎራዶ የትምህርት ስኬት መለኪያዎች (CMAS) |
| 9ኛ ክፍል | PSAT 9 |
| 10ኛ ክፍል | PSAT 10 |
| 11ኛ ክፍል | SAT፣ CMAS ሳይንስ፣ CMAS ሶሻል ስተዲስ |

የPSAT ፈተና ተማሪዎች ወሳኝ ለሆነው የኮሌጅ መግባ ፈተና ለሆነው እና በአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ለሚወሰደው የSAT (የትምህርታዊ ዝንባሌ ፈተና) እንዲዘጋጁ ይረዳቸዋል። SAT በአብዛኛዎቹ ኮሌጆች ተማሪን ለመቀበል እና የነፃ-ትምህርት ዕድል (ስኮላርሺፕ) ለመስጠት የሚጠቀሙበት ስለሆነ ለተማሪዎች PSAT መውሰዱ ለኮሌጅ ለመዘጋጀት ቁልፍ እርምጃ ነው። PSAT በጥያቄዎች ይዘት እና ቅርጸት ከSAT ጋር ተመሳሳይ ሰለሆነ የPSAT ውጤቶች ለወደፊቱ የSAT ውጤት ትንበያ ይሰጣሉ።

## ልጄ የሚፈተነው/የምትፈተነው መቼ ነው?

PSAT በወረቀት እና እርሳስ ቅርጸትን በመጠቀም ኤፕሪል ውስጥ ይሰጣል። ፈተናው በግምት 3 ሰዓት ያህል የሚወስድ ነው።  ስለ ዝርዝር የፈተና የጊዜ-ሰሌዳ መረጃ ለማግኘት የልጅዎን ት/ቤት ይጠይቁ።

## ልጄ ምን ውጤት(ቶች) ይሰጠዋል/ታል?

ተማሪዎች በ320 እና 1520 መካከል የሆኑ ውጤቶችን ያገኛሉ። ይህ ውጤት ተማሪዎች በሒሳብ እና ንባብ እና ጽሕፈት ክፍሎች የሚኖራቸውን ዕድገት/ለውጥ ጥምር ውጤቶች ይወክላል። ውጤቶቹ በተማሪ ውጤት መግለጫዎች (ትራንስክሪፕቶች) የማይካተቱ ሲሆኑ የትምህርት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለተማሪዎች በፖስታ ይላካል።

## እነዚህ ውጤቶች እንዴት ጥቅም ላይ ይውላሉ?

PSAT እና SAT ለመማር-ማስተማሩ ግብረመልስ ለመስጠት፣ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ ግቦቻቸውን እያሳኩ መሆናቸውን እና ኮሌጅ ለመግባት ትክክለኛ ጎዳና ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ መምህራን እገዛ ያደርጉላቸው ዘንድ ወደኋላ የቀሩትን ለመለየት እና ለከፍተኛ ፕሮግራም ትምህርት (AP ኮርስወርክ) የተማሪዎችን ዝግጁነት አመላካች ለመስጠት የተቀረጹ ናቸው። የተማሪዎች ውጤቶች ከክፍል ውጤቶች ጋር አይደመሩም፤ በኮሌጅ ውጤት መግለጫዎች (ትራንስክሪፕቶች) ላይም አይካተቱም።

## ተጨማሪ መረጃ

በልጅዎ ትምህርት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ እናበረታታዎታለን። ልጅዎን በቤት ውስጥ ማገዝ ስለሚችሉባቸው መንገዶች እና ሊገኙ ስለሚችሉ የፈተና እገዛዎች (አቅርቦቶች) ለመጠየቅ ወደኋላ እንዳይሉ እባክዎ።

**ለተጨማሪ መረጃ፡- ምዘናዎች**
የሚከተሉትን ድር ጣቢያዎች ይጎብኙ፡-

- http://assessments.dpsk12.org
- http://parents.collegeboard.org

**ግብዓቶች፡- PSAT እና SAT**

ለአዲስ SAT የየዕለት ልምምድ | ኮሌጅ ቦርድ

- በየዕለቱ የናሙና ጥያቄዎችን ያግኙ፤ ወዲያውኑም ግብረ-መልስ ያግኙ።
- ተማሪዎች በመደበኛነት እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል።
- ተማሪዎች የታተሙ የመልስ መስጫ ወረቀቶችን ተጠቅመው የPSAT ወይም የSAT የልምምድ ፈተናዎችን መሥራት ይችላሉ። ከዚያም ፎቶ አንስተው "ስካን እና ስኮር" የሚለውን ማስፈጸሚያ /function/ መጠቀም ይችላሉ።

ኦፊሲያላዊ የPSAT ልምምድ | Khan አካዳሚ

- ተማሪዎች ለመለያ (አካውንት) ይመዘገቡ እና በPSAT እና SAT ውጤቶቻቸው መሠረት ግለሰባዊ የሆኑ ሊያሻሽሉ የሚገባቸው መስኮች ላይ ምክር ወይም ጥቆማ ያገኛሉ።
- ሙሉ ርዝመት ያላቸው የልምምድ ፈተናዎች፣ የምርመራ ሙከራዎች /diagnostic quizzes/፣ የየዕለት የልምምድ ጥያቄዎች እና ለተወሰኑ የፈተናው ዘርፎች የታለሙ የመዘጋጃ ግብዓቶች በKhan አካዳሚ ድር ጣቢያ በነፃ ይገኛሉ፡- https://www.khanacademy.org/mission/sat.

PSAT ልምምድ | የወንዶችና ሴቶች ልጆች ክበብ

- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ተማሪዎች ከSAT እና PSAT የመስመር ላይ ግብዓቶች ጋር ለማገናኘት ከወንዶችና ሴቶች ልጆች ክበብ /oys & Girls Club/ ጋር አጋርነትን ፈጥረናል።

ስለምዘናዎቹ ጥያቄዎች ወይም ሀሳቦች ካሉዎ፣ የልጅዎን ት/ቤት በቀጥታ ያነጋግሩ ወይም የቤተሰብ የምርጫ ክልል /Constituency/ አገልግሎትን በ(720) 423-3054 ደውለው ያነጋግሩ።